የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት

ETHIOPIAN INTELLECTUAL PROPERTY OFFICE

የውስጥ ለውስጥ ማስታወሻ

INTER OFFICE MEMO

ቀን 8/08/2012 ዓ.ም.

ለ
ፓተንት ጥበቃና ቴክኖሎጂ ሽግግር ዳይሬክቶሬት
ንግድ ምልክት ኢ/ን/ጥበቃና ልማት ዳይሬክቶሬት
ኮፒራይትና የማህበረሰቦች ዕዉቀት ጥበቃና ልማት ዳይሬክቶሬት
አዕምሯዊ ንብረት ልማት ዳይሬክቶሬት
ለውጥና መልካም አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
ግዥ፣ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
አዕምሯዊ ንብረት ይግባኝ ሰሚ ዳይሬክቶሬት
ህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
ሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
ክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ዴስክ ማስተባበሪያ
ዕቅድ ዝግጅት ክትትልና ግምገማ ቡድን

ከ ም/ዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት

አዲስ አበባ

## ጉዳዩ፡-የንግድ ምልክት ማመልከቻ ምርመራ መመሪያ ስለመላክ፤

የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት የንግድ ምልክት የምርመራ ሥራ የሚመራበትን መመሪያ በማስጠናት እና በማስተቸት ተግባራዊ እንዲሆን ፀድቋል ፡፡

ስለዚህ የንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻ ምርመራ መመሪያ ቁጥር 647/2013 ~~3/2012~~ ዓ.ም.ተግባራዊ እንድታደርጉ ቅጂዉን ከዚህ ሸኚ ደብዳቤ ጋር 19 ገጽ አያይዘን የላከን መሆኑን እናሳዉቃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ፤

- ለዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት
- ለአማካሪ

የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት

# የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽህፈት ቤት

## የንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻ ምርመራ መመሪያ

## መመሪያ ቁጥር 647/2013



የጽ/ቤቱ የንግድ ምልክት ማመልከቻ የስርአት እና የስረ-ነገር መርማሪዎች የምርመራ ስራቸውን የሚመሩበትን ዝርዝር መምሪያ ማውጣት በማስፈለጉ እንዲሁም የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አገልግሎትን ግልጽ፣ተገማችና ቀልጣፋ ለማድረግ እንዲሁም እና ተጠያቂነት የሰፈነበት ስርአት መዘርጋት በማስፈለጉ ይህ የንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻ ምርመራ መመሪያ በንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 273/2005 አንቀጽ 59 መሠረት ተደንግጓል።

### ክፍል 1

### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. አጭር ርእስ

ይህ መመሪያ "የንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻ ምርመራ መመሪያ ቁጥር 647/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

1/ "አዋጅ" ማለት የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/1998 ነው፤

2/ "ደንብ" ማለት የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 273/2005 ነው፤

3/ "ማመልከቻ" ማለት የንግድ ምልክትን ለማስመዝገብ በጽ/ቤቱ የተዘጋጀውና ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ ተደርጎ የተያያዘው የንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻ ቅጽ ነው፤

4/ "መርማሪ" ማለት ለጽ/ቤቱ የቀረበን የንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻ በአዋጁ፣ በደንቡና በዚህና በሌሎች አግባብነት ባላቸው መመርያዎች የተደነገጉትን የፎርማሊቲና የሥረነገር መስፈርቶችን ስለማሟላቱ ምርመራ የሚያከናውን ባለሙያ ወይም የቡድን መሪ ነው፤

5/ "ዳይሬክቶሬት" ማለት በጽ/ቤቱ ውስ የተቋቋመው የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ ዳይሬክቶሬት ነው፤



6/ በአእምሯዊ ንብረት ትሪቡናል ማቋቋሚያ መመሪያ ቁጥር 1/2010 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (6) ላይ ለአእምሯዊ ንብረት ትሪቡናል የተሰጠው ትርጓሜ በዚህ መመሪያ በተመሳሳይነት ትሪቡናል ለሚለው ትርጓሜ ተፈጻሚ ይሆናል፤

3. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ ለምዝገባ የቀረበ የንግድ ምልክት ማመልከቻ በአዋጁ፣በደንቡ እና በዚህ መመሪያ የሰፈሩ መስፈርቶችን አሟልቶ መቅረቡን በማረጋገጥ፤ቀልጣፋና ውጤታማ ምርመራ በማድረግ ምዝገባን ማከናወን ይሆናል።

4. መርሆች

የመመሪያው መሠረታዊ መርሆዎች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

1/ የንግድ ምልክት ምዝገባ ለንግድ ምልክት ባለቤቱ በንግድ ምልክቱ ላይ የብቸኛ ተጠቃሚነት መብት እንዲያስገኝለት ለማድረግ፡፡

2/ የንግድ ምልክት ምዝገባ የጠቅላላውን ሕዝብ እና የግለሰብ ነጋዴዎችን ጥቅም የሚጠብቅ ይሆናል፡፡

3/ ከሌላ ሰው ቀዳሚ የንግድ ምልክት ጋር አንድ ዓይነት የሆነ ወይም መሳከርን ሊያስከትል የሚችል ተመሳሳይነት ያለው የንግድ ምልክት አይመዘገብም፡፡

4/ የንግድ ምልክት ምዝገባ ከምዝገባው በፊት በቅን ልቦናው ስሙን፣የሥራ ቦታውን ስያሜ፣የሚያመርትበትን ቦታ፤የዕቃውን ባህርይ ወይም ዓይነት ለመግለጽ የሚጠቀምባቸውን ቃላት ወይም ምስሎች ጥቅም ላይ ያዋለን ማንኛውንም ሰው መብት አይነካም፡፡

5. ስለቀዳሚ የንግድ ምልክት

1/ አመልካቹ በውጭ አገር ያስመዘገበው የንግድ ምልክት የምዝገባ ማመልከቻ ተቀባይነት ማግኘት፣ውድቅ መሆን ወይም የተቋወ መሆን በኢትዮጵያ የቀዳሚነት

መብት ለማግኘት ካቀረበው የቀዳሚነት መብት ማመልከቻ ሁኔታ ጋር ተያያዥነት አይኖረውም።



2/የቀዳሚት ጠያቂው አመልካች በደንቡ አንቀጽ 13 የተቀመጠውን ቅድመ ሁኔታ አሟልቶ ካልተገኘ ማመልከቻው እንደማንኛውም የቀዳሚነት ቀን እንደማይጠይቁ ማመልከቻዎች ተቆጥሮ በደንቡ አንቀጽ 6 መሰረት ማመልከቻው ለጽ/ቤቱ ገቢ የሆነበትን ቀንና ሰዓት መሰረት በማድረግ የምዝገባው ሂደት እንዲቀጥል ይደረጋል።

## ክፍል 2

## የንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻ አቀራረብ፣ ስለሚይዛቸው መግለጫዎችና ተያይዘው መቅረብ ስላለባቸው ሰነዶች

6. የማመልከቻ አቀራረብ

በአዋጁና በደንቡ የሰፈሩት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ለንግድ ምልክት ምዝገባ የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን ዝርዝሮች የሚያካትት ይሆናል፡-

1/ የአመልካቹን ስም፣ ዜግነት እና የተሟላ አድራሻ፤

2/ የንግድ ምልክቱን ወካይ ናሙና ወይም ምስል፤

3/ እ.ኤ.አ በ1957 በኒስ እሰም አቀፍ ስምምነት መሠረት ወቅታዊ የዓለም አቀፍ የዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ምደባ መሠረት በማድረግ የምዝገባ ማመልከቻው በቀረበበት ዓ.ም ጽ/ቤቱ ለምዝገባ የሚጠቀምበትንና የተሻሻለውን የዓለም አቀፍ የእቃዎች ወይም አገልግሎቶች ምድብ፤

4/ በማመልከቻው የቀረቡ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ጥቅም ላይ የዋሉ ወይም እንዲውሉ የታሰበ ስለመሆኑ መግለጫ፤

5/ የቀዳሚነት መብት ጥያቄ የሚቀርብ ሲሆን ይህንኑ የሚያመለክት ዝርዝር፤

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የሚቀርበው ናሙና ለምዝገባ የቀረበው የንግድ ምልክት እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል በማያሻማ ሁኔታ ለመረዳት የሚያስችል መሆን አለበት፡፡

7. የንግድ ምልክት ሥዕላዊ መግለጫ

1/ ሥዕላዊ ወይም ሥዕላዊ የሆኑ ነገሮችን የያዙ የንግድ ምልክቶች ትክክለኛ ናሙና ሊቀርብና ግልፅ መግለጫ ሊሰጥባቸው ይገባል፡፡

2/ ከምዝገባ ማመልከቻ ጋር የሚቀርብ የንግድ ምልክት ሥዕላዊ መግለጫ በደንቡ አንቀጽ 11 መሠረት መቅረብ አለበት፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ስለንግድ ምልክቱ የሚቀርቡ ናሙናዎች የትክክለኛው የንግድ ምልክት ወካይ መሆናቸውን መርማሪው ማረጋገጥ አለበት፡፡

4/ አመልካቹ የንግድ ምልክቱን በዕቃዎቹ ወይም በአገልግሎቶቹ የንግድ ምልክት ላይ የሚያቀርባቸው ናሙና እና ትክክለኛ መግለጫ የንግድ ምልክቱን በሚጠቀምበት አግባብ በትክክል ሳያቀርብ ከቀረ የንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻው ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

8. ቀለምና የቀለም ቅንጅት ያላቸው ምልክቶች

1/ ለምዝገባ የቀረበው የንግድ ምልክት የቀለም ቅንጅት፣ሥዕል፣ የስዕል እና/ወይም የቀለም ቅንጅት ያላቸው የንግድ ምልክት እንዲሁም ስእላዊ መግለጫ የያዘ በሆነ ጊዜ፡-

ሀ. የሚቀርቡት ናሙናዎች የትክክለኛው የንግድ ምልክት ወካይ መሆናቸውን፤

ለ. እያንዳንዱ ቀለም በምልክቱ ውስጥ የሚገኝበት ቦታ የተገለፀ መሆኑን እና

ሐ. የንግድ ምልክቱ የቀለም ቅንጅት ወይም መለያ ባህሪው ነው የተባለበት ምክንያት ላይ መግለጫ የተሰጠበት መሆኑን መርማሪው ማረጋገጥ አለበት፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለተመለከቱት የንግድ ምልክቶች የሚቀርቡ

ናሙናዎች የንግድ ምልክቶቹ በዕቃዎቹ ወይም በአገልግሎቶቹ ላይ ጥቅም ላይ በዋሉባቸው አኳኋን ሆነው መቅረብ አለባቸው፡፡

3/ የሚቀርቡ መግለጫዎች በግልፅና በማያሻማ ሁኔታ ተጽፈው የቀረቡ መሆኑን መርማሪው ማረጋገጥ አለበት፡፡

9. ስለዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች መግለጫ

1/ የንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻ የንግድ ምልክቱ ጥቅም ላይ የሚውልባቸውን ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች መግለፅ አለበት፡፡

2/ የዕቃዎቹ ወይም የአገልግሎቶቹ መግለጫ በተመዘገበው የንግድ ምልክት ላይ ያለውን የመብት ወሰን የሚያመለክት መሆን አለበት፡፡

3/ አመልካቹ በማመልከቻው ያቀረበው የዕቃዎቹ ወይም የአገልግሎቶቹ መግለጫ በጅምላ ሳይሆን አመልካቹ እየሠራባቸው ያሉትን ወይም ወደፊት ታሳቢ ያደረጋቸውን ገልፆ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

10. የዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ምድብ

1/ ጽ/ቤቱ የንግድ ምልክቶችን የሚመዘግበው በ1957 የኒስ ዓለም አቀፍ የዕቃዎችና አገልግሎቶችምድብ መሠረት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (3) ላይ በተመለከተው ሁኔታ መሆን አለበት፡፡

2/ አመልካቹ ላስመዘገበው የንግድ ምልክት ጥበቃ የሚያገኘው በማመልከቻው ቅጽ ላይ ለተገለጹት ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ብቻ ይሆናል፡፡

3/ የቀረበው ማመልከቻ በአዋጁ አንቀጽ 8 (3) (ለ)መሠረት ተሟልቶ የቀረበ መሆኑን መርማሪው ማረጋገጥ አለበት፡፡

11. የብቸኛ ተጠቃሚነት መብት ያለመጠየቅ መግለጫ

1/ በምዝገባ ማመልከቻው የቀረበው የንግድ ምልክት ጥበቃ የማይደረግላቸውን ነገሮች የያዘ ከሆነ አመልካቹ በእነዚሁ ነገሮች ላይ መብት የማይጠይቅ ስለመሆኑ መግለጫ እንዲሰጥ መደረግ አለበት፡፡

2/ አመልካቹ በንግድ ምልክቱ ተዘርዝረው ከቀረቡት ነገሮች መካከል የብቸኛ ተጠቃሚነት መብት ያለመጠየቅ ወይም በምዝገባ በተገኘው መብት ላይ ገደብ እንዲጣልበት ለመስማማት የሚያስችለው ሲሆን መብቱም በዚያው ልክ ገደብ የተጣለበት ይሆናል፡፡

3/ የብቸኛ ተጠቃሚነት መብት ያለመጠየቅ ፎርማሊቲ የ 1957ቱን የኒስ ዓለም አቀፍ የዕቃዎችና አገልግሎቶች ምድብ ሥርዐት ተከትሎ የሚፈጸም ይሆናል፡፡

4/ በአዋጁ መሠረት ለምዝገባ ተገቢነት ባለው የንግድ ምልክት ውስጥ የዕቃው ወይም የአገልግሎቱ ስም ወይም ባህርይውን ወይም የሚገኝበትን ቦታ የሚገልጸው ክፍል ሊመዘገብ አይችልም፡፡

5/ ንግድ ምልክቱ የብቸኛ ተጠቃሚነት መብት የማይጠየቅበትን ክፍል የያዘ ቢሆንም ለምዝገባ የቀረበው አጠቃላይ ምልክቱ ለምዝገባ ተገቢነት ያለው መሆኑ/አለመሆኑ/ በቅድሚያ በምርመራ መረጋገጥ አለበት፡፡

6/ አመልካቹ እንዲመዘገብለት ያቀረበው የንግድ ምልክት ለምዝገባ ተገቢነት የሌለው ከሆነ የብቸኛ ተጠቃሚነት መብት ያለመጠየቅ መግለጫ በሚል ምክንያት የንግድ ምልክቱ አይመዘገብለትም፡፡

7/ የምስል ቅንጅቶች ወይም የተውጣጡ ነገሮችን በያዘ የንግድ ምልክት ውስጥ የምዝገባ ማመልከቻ የቀረበበት የንግድ ምልክት የብቸኛ ተጠቃሚነት መብት ከማይጠየቅበት ክፍል በላይ ደምቆ መለየት በሚያስችል ሁኔታ የጎላ ሲሆን ምልክቱ ሊመዘገብ ይችላል፡፡

8/ ለምዝገባ የቀረበው የንግድ ምልክት ከያዛቸው ምስሎች መካከል ልዩ ያልሆነው ምስል ጥበቃ ሊደረግለት የማያስችል በሆነ ጊዜ አመልካቹ ልዩ ያልሆነውን የምልክት ክፍል የብቸኛ ተጠቃሚነት መብት የማይጠይቅበት ስለመሆኑ መግለጫ እንዲሰጥበት መደረግ አለበት፡፡

9/ የብቸኛ ተጠቃሚነት መብት ያለመጠየቅ መግለጫ ወይም ገደብ የሚደረግባቸው ሁኔታዎች መግለጫ ለንግድ ምልክት ባለቤት በሚሰጥ የንግድ ምልክት የምስክር ወረቀት ላይ መጻፍ አለበት፡፡

12. ከንግድ ምልክት ማመልከቻ ጋር ተያይዘው መቅረብ ስላለባቸው ሰነዶች

1/ የውጭ ሀገር አመልካቾች በየሀገራቸው ስልጣን ባለው አካል የተረጋገጠ የንግድ ምልክት ምዝገባ የምስክር ወረቀት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

2/ የውጭ አገር ዜጋ የሆነ አመልካች ነዋሪነቱ ኢትዮጵያ ውስጥ የሆነ እና ከዕ/ቤቱ

የንግድ ምልክት ወኪልነት ፍቃድ የተሰጠው ወኪል ስለመሰየሙ የሚያሳይ ማስረጃ ፤

3/ በአዋጁ አንቀጽ 10 እና በደንቡ አንቀጽ 13 መሠረት ከንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻ ጋር ተያይዞ ለጽ/ቤቱ የሚቀርብ ሰነድ አግባብነት ባለው የሀገር ውስጥ ተቋም ተረጋግጦ መቅረብ አለበት፡፡



4/ ታህሳስ 2006 ዓ.ም የንግድ ምልክትን ለማስመዝገብ የወጣ ተጨማሪ መመሪያ አንቀጽ 3 በዚህ አንቀጽ ተተክቷል፡፡

## ክፍል 3

## ስለማመልከቻ ምርመራ

13. የምርመራ አፈጻጸም

1/ በደንቡ አንቀጽ 6 መሠረት የሰነዶች መረክብና መለያ ቁጥር መስጠት ከተከናወነ በኋላ የንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻው መመርመር አለበት፡፡

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀዳሚነት መብትን ለማረጋገጥ በሚያስችል ሁኔታ የንግድ ምልክት ማመልከቻው የቀረበበት ቀንና ሰዓት መመዝገቡንና ሰነዶቹ ተሟልተው የቀረቡ መሆኑን መርማሪው ማረጋገጥ አለበት፡፡

3/ ለምዝገባ የቀረበው ማመልከቻ በአዋጁ፣በደንቡና በዚህ መመሪያ የተቀመጡ መመዘኛዎችን የሚያሟላ መሆኑን ለማረጋገጥ መርማሪው የሚያከናውነው ምርመራ እንደተጠበቀ ሆኖ ለምዝገባ በቀረበው የንግድ ምልክት ላይ ጽ/ቤቱ ፍለጋና ምርመራ ያደርጋል፡፡

4/ ጽ/ቤቱ የንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻን ተቀብሎ በሚያደርገው ምርመራ፡-

ሀ. የቀረበው የንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻ በአዋጁና በደንቡ ድንጋጌዎች መሠረት ብቁ መሆኑንና ምዝገባን የማያስከለክል መሆኑን፣ወይም

ለ. ለተቃውሞ ጥሪ ሲደረግ የቀረበው የንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻ በአዋጁና በደንቡ ውስጥ አግባብነት ባላቸው ድንጋጌዎች መሠረት ምዝገባው ሊከለከል ይገባል ብሎ ተከራካሪ ተቃውሞ ሲያቀርብ፣በቀረበው ተቃውሞ መሠረት መርምሮ

ውሳኔ መስጠት አለበት።

5/ ለምዝገባ የቀረበ የንግድ ምልክት በአዋጁ በተሰጠው ትርጉም መሠረት መስፈርቶችን ማሟላቱ በመርማሪው መረጋገጥ አለበት።



14. ምርመራ ሲከናወን ታሳቢ ስለሚደረጉ ሁኔታዎች

1/ ልዩነትን የማያመለክቱ ምልክቶች ወይም የመለያነት ባህሪይ የላቸውም የሚባሉ ምልክቶች በአዋጁ አንቀጽ 6 (1) (ሐ) (ሠ) እና (ረ) ድንጋጌዎች መሠረት ልዩነትን የማያመለክቱ ምልክቶች፣ገላጭ የሆኑና በንግድ ሥራ ውስጥ የተለመዱ፣በጋራ መግባቢያ ቋንቋነት የሚያገለግሉ ምልክቶች በመሆናቸው ምዝገባ የሚከለከልባቸው ምክንያቶች ናቸው።

2/ ምልክቱ በማመልከቻው የተመለከቱትን ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች የራሳቸውን ዓይነት፣ባህሪይ፣ስም ወይም መጠን የሚያመለክቱ ሆነው ከተገኙ ገላጭ በመሆናቸው ምልክቶቹ ልዩ ምልክትነት አይኖራቸውም።

3/ በዕቃው ጠቀሜታ ወይም ተግባር ላይ ቀጥተኛ ገለፃ የሚያደርጉ ወይም በአገልግሎቱ ምክንያት ወይም የዕቃው ሽግች በዕቃው የሚያደርገውን የሚያመለክት ወይም ዕቃው በአገልግሎት ላይ ሲውል የሚታዩ ውጤቶችን የሚገልፁ ቃላትን የያዘ የንግድ ምልክት አይመዘገብም።

4/ በማመልከቻ የቀረበው የንግድ ምልክት የተለመደና የጋራ መጠሪያ ስለመሆኑ ማሳያ ይሆናሉ የተባሉት ምክንያቶች በጽሑፍ ተዘጋጅቶ በሚመለከተው የሥራ ኃላፊ ተፈርሞ ለአመልካቹ መስጠት አለበት።

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት የንግድ ምልክቱን በጋራ መግባቢያ ቋንቋነት እጥቅም ላይ እንደዋለ ለማወቅ በልዩ ልዩ ሁኔታ በሕብረተሰቡ ውስጥ በስፋት በዋሉ መገናኛ ዘዴዎች ስለዕቃዎቹ ወይም ስለአገልግሎቶቹ የተነገሩ ማስታወቂያዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ የተወሰኑ መሆን አለባቸው።

6/ መርማሪው የአዋጁን አንቀጽ 6(1) (ሐ) ፣ (ሠ) እና (ረ) መሠረት አድርጎ በዚህ አንቀጽ መሠረት ምርመራውን ካከናወነ በኋላ የንግድ ምልክቱ አይመዘገብም የሚል

ከሆነ የማይመዘገብበትን ምክንያት በጽሑፍ አዘጋጅቶ ለሚመለከተው ኃላፊ ማቅረብ አለበት፡፡

15. በቅን ልቦና ጥቅም ላይ ስለዋሉ የንግድ ምልክቶች



1/ በቅን ልቦና ለንግድ ተግባር በንግድ ምልክትነት ጥቅም ላይ የዋሉ ምልክቶች ጥቅም ላይ መዋላቸውን በማስረዳት በመዝገብ እንዲገቡ ጥያቄ ሊቀርብ ይችላል፡፡

2/ የንግድ ምልክቱ መለያ ባለመሆን ወይም የዕቃውን ባህሪይ የሚገልጽ ወይም የቤተዘመድ ስም፣የመልክዓ ምድር ስም ወይም የጋራ መግባቢያ ቋንቋ ሆኖ በተፈጥሮው ለንግድ ምልክትነት ሊመዘገብ የማይገባው የንግድ ምልክት ጥቅም ላይ በመዋሉ ምክንያት ሊመዘገብ ይችላል፡፡

3/ ስለሆነም ምልክቱ በመርህ የማይመዘገብ ቢሆንም ጥቅም ላይ በመዋሉ ምክንያት የተለየ ምልክት ወይም ታዋቂነትን ያገኘ በመሆኑ ምዝገባ ሊከለከል አይችልም፡፡

16. የመፈክር ንግድ ምልክቶች

ለሚወክሉት እቃ እና አገልግሎት ልዩ ባህሪ ያላቸው እና በቀጥታ ገላጭ እስካልሆኑ ድረስ መፈክር በመሆናቸው ብቻ ምዝገባ ሊከለከሉ አይችሉም፡፡

17. የሕዝብ ሰላምን ወይም ሥነምግባርን የሚጻረር የንግድ ምልክት

1/ በአዋጁ አንቀጽ 6(1) (መ) መሠረት የህዝብን ሰላም ወይም ሥነምግባር የሚጻረር ለምዝገባ የቀረበ የንግድ ምልክት ማመልከቻ ተቀባይነት የሌለው ሲሆን በተለይም፡-

ሀ. የሕዝብን ወግ እና ልማድ የሚቃረን የንግድ ምልክት፤

ለ. ኃይማኖታዊ ተምሳሌትነት ያላቸው፣ የምግባረ ሰናይ ድርጅቶችን የሚመለከቱ፣ ባህላዊና የትምህርት ማህበራትን እሴቶችን ሊያናጉ የሚችሉ የንግድ ምልክቶች፤

ሐ. የቤተሰብ ተቋምን እና ማህበራዊ እሴቶችን የሚያናጉ የንግድ ምልክቶች፤

በንግድ ምልክትነት አይመዘገቡም፡፡

2/ ለምዝገባ የቀረበ ማመልከቻ የንግድ ምልክት ፅሑፎች፣ምስሎች፣ ሰዋሰዋዊ ሀረጎች

የሚያስተላልፉትን መልዕክት ከሕዝብ ሰላምና ሥነምግባር አንፃር መርማሪው መመርመር አለበት፡፡



3/ አሉታዊ መልእክትን ሊያስተላልፍ የሚችል ኃይማኖታዊ ትርጉም ያለው ቃል ወይም ከፍተኛ የኃይማኖት መሪዎች ስም ወይም ማዕረግ ለእቃዎች ወይም ለአገልግሎቶች በንግድ ምልክትነት አይመዘገብም፡፡

4/ መርማሪው ዓቅሙ እስከፈቀደ ድረስ የቋንቋ እና የባህል ልዩነቶችን ተከትሉ በተለያዩ አካባቢዎች የሚነገሩ ቃላት በሌሎች ቋንቋ ተናጋሪዎች መካከል ያላቸውም ትርጉም የሕዝብን መልካም ሥነምግባር የሚያናጉ አለመሆናቸውን ከቀረበው የእቃዎች ወይም አገልግሎቶች ንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻ አንጻር መመርመር አለበት፡፡

5/ በሌሎች ሕጎች ሕገወጥ የተባሉ ድርጊቶች ወይም ከባህል ወይም ከታሪክ አንጻር ሰላምን የሚያናጉ የንግድ ምልክቶች አይመዘገቡም፡፡

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት የሚቀርብ የንግድ ምልክት በሌላ የኢትዮጵያ ቋንቋ ትርጉም ያለው ነው ብሎ ከጠረጠረ መርማሪው አመልካቹ የንግድ ምልክቱን ትርጉም በቃለ መሓላ እንዲያረጋግጥ ማድረግ አለበት፡፡

7/ ቃለ መሓላውን የሚሰጠው ሰው ጽ/ቤቱ በሚያዘጋጀው የቃለ መሓላ አሰጣጥ ሥነሥርዓት መሠረት ይሆናል፡፡

18. ማመልከቻ ማቅረብ ስለሚገባው ሰው

ማንኛውም የንግድ ምልክት ባለቤት ወይም በሕግ መሠረት በንግድ ምልክት ባለቤቱ የተወከለ ሰው የንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

## ክፍል 4

## የምርመራ መስፈርቶች

19. በምርመራ ወቅት ከግምት ስለሚገቡ ሁኔታዎች

ለምዝገባ የቀረበ የንግድ ምልክት ተመሳሳይነትን ወይም አንድነትን ለመወሰን በአዋጁና በደንቡ ከተደነገጉት መስፈርቶች በተጨማሪ አንድ መርማሪ ከዚህ በታች የተመለከቱትን መስፈርቶች ከግምት ማስገባት አለበት፡፡

20. አንድ ዓይነት የንግድ ምልክቶች

1/ አንድ የንግድ ምልክት ከሌላ የንግድ ምልክት ጋር አንድ ዓይነት ነው እንዲባል የንግድ ምልክቱ ያለምንም ለውጥ ወይም ሌላ ነገር ሳይታከልበት ሌላኛው የንግድ ምልክት የያዛቸውን ሁሉ ነገሮች አስመስሎ ሲይዝ ወይም በንግድ ምልክቱ በሙሉ ያሉት ጥቃቅን ልዩነቶች መደበኛ በሆነው ሸማች ህብረተሰብ ዕይታ ውስጥ ሳይገቡ የሚታለፉ ሲሆን ነው፡፡ጥቃቅን ወይም ዝርዝር የሆኑ ልዩነቶች ግምት ውስጥ ሳይገቡ የንግድ ምልክቶቹ ወጥ ሆነው ሲታዩ የተቀራረቡ ከሆነ አንድ ዓይነት ሊባሉ ይቻላሉ፡፡

2/ ሆኖም የንግድ ምልክት አንድ ዐይነት መሆን አለመሆኑን ለመወሰን ዕይታን፣ ድምጸትንና የትርጉም ተመሳሳይነትን ጨምሮ ምልክቱ የሚፈጥረውን አጠቃላይ ስሜት መሠረት አድርጎ መሆን አለበት፡፡

3/ አንድ የንግድ ምልክት ከቀዳሚ የንግድ ምልክት ጋር የተቀራረበ ተመሳሳይነት የሚኖረው ከሆነና የንግድ ምልክቶቹ ጥቅም ላይ የዋሉት ለተመሳሳይ ምርቶች ከሆነ ተመሳሳይነት ያላቸው በመሆኑ መሳከርን ሊያስከትሉ ይችላል፡፡

21. የንፅፅር ዘዴ

1/ በንግድ ምልክቶች መካከል ተመሳሳይነት እንዳለ ለማየት ምስሎቹ፣ቃላት ፊደሎች ወይም የንግድ ምልክቱ መነባፀር ያለባቸው ሸማቹ ህብረተሰብ መደበኛ ግብይት በሚፈጽምበት ዐይነት መሆን አለበት፡፡

2/ መርማሪው ተመሳሳይነትን ወይም አንድ ዐይነት መሆንን ሲመረምር ሸማቾች እንደ ዕቃው ወይም አገልግሎቱ ዓይነት የተለያዩና ዕቃን ለመሸመት የሸማች የመደበኛ ዕውቀት ደረጃ እንደዕቃው ዐይነት የተለያዩ መሆኑን ከግምት ማስገባት ይኖርበታል፡፡

22. የቃላት ወይም የፊደላት አወቃቀር

1/ መርማሪው የንግድ ምልክቶችን ሲመረምር፦

ሀ. ከጋራ መድረሻ ቃላት ይልቅ የጋራ መነሻ ቃላት የበለጠ መሳከር ሊፈጥሩ የሚችሉ መሆኑን፤

ለ. የመድረሻ ቃላታቸው ተመሳሳይ ከሆኑት ይልቅ የመነሻ ቃላታቸው ተመሳሳይ ወይም አንድ ዓይነት የሆኑት የበለጠ አሳሳች መሆናቸውን፤

ሐ. የተለያዩ መነሻ ፊደሎች ካሏቸው አጫጭር ቃላት ይልቅ የጋራ ወይም ተመሳሳይ መነሻ ያሏቸው ረዣዥም ቃላትና በፊደል ተለያይተው በእይታ የሚመሳሰሉ ወይም በእይታ ተለያይተው በፊደል የሚመሳሰሉ የበለጠ ሊያሳክሩ የሚችሉ መሆናቸውን፤ከግምት ማስገባት ይኖርበታል፡፡

2/ ምልክቱን በአጠቃላይ በማየት ምርመራ የሚደረግ ሲሆን የንግድ ምልክቱ ፊደላት አቀማመጥ ተመሳሳይነትን ወይም አንድነትን የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ መርማሪው የንግድ ምልክቶችን በማነጻጸር ከመመርመር አያግደውም፡፡

23. ገላጭና ልዩ ምልክቶች

1/ ከተመዘገቡባቸው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ጋር የተዛመደ ትርጉም ካላቸው የንግድ ምልክቶች ይልቅ (በፈጠራ ተሰርተው ጥቅም ላይ የዋሉ) ምልክቶች መሳከርን የማያስከትሉ መሆኑን መርማሪው ከግምት ማስገባት አለበት፡፡

2/ ተመሳሳይ ነገሮችን የሚጋሩ የንግድ ምልክቶች በሚነጻጸሩበት ወቅት የእነዚህን ዓይነት ተመሳሳይ ነገሮችን የሚጋሩ ሌሎች በመዝገብ የገቡና በሌሎች ባለመብቶች ጥቅም ላይ የዋሉ የንግድ ምልክቶች መኖራቸው መታወቅ ይኖርበታል፡፡

24. የምልክቶች መመሳሰል

መመሳሰልን ለመወሰን የሚከተሉት ከግምት መግባት አለባቸው፦

1/ የንግድ ምልክቱ ሲመረመር መደበኛ እውቀትና መጠነኛ ትውስታ ባለው ሰው እይታ ግምት መውሰድ ይገባል፡፡

2/ አጠቃላይ የቃላቱ አቀማመጥ እና የድምፅ ተመሳሳይነት እንዲሁም በሁለቱ ምልክቶች ጀርባ ያለው አሳብ መሳከር የሚፈጥር ስለመሆኑ ምርመራ ማድረግ ይገባል፡፡

25. በዕቃዎች መካከል ተመሳሳይነት መኖሩን ለመወሰን የሚከተሉት ሁኔታዎች ግምት ውስጥ ይገባሉ፦

1/ ተመሳሳይ ተግባር ወይም ጥቅም ያላቸው መሆኑ፤

2/ ተመሳሳይ የገበያ ተፈላጊነት ወይም የግብይት ሰንሰለት ወይም ተመሳሳይ የገበያ ማዕከል ያላቸው መሆኑ።

26. በአገልግሎቶች መካከል ተመሳሳይነት መኖሩን ለመወሰን የሚከተሉት ሁኔታዎች ግምት ውስጥ ይገባሉ፡፡

1/ ተመሳሳይ ባህሪይ ያላቸው አገልግሎቶች መሆናቸው፤

2/ አገልግሎቶቹ ተመሳሳይ ዓላማ ወይም ጥቅም ያላቸው መሆኑ፤

3/ የአገልግሎቶቹ ተጠቃሚ ተመሳሳይ መሆኑ።

27. በቀዳሚ የንግድ ምልክት ምክንያት ምዝገባ የሚከለከልባቸው መስፈርቶች

1/ ቀዳሚ የንግድ ምልክት ያለው መልካም ስምና ዝና ለምዝገባ የቀረበ የንግድ ምልክት እንዳይመዘገብ ምክንያት ይሆናል።

2/ ለምዝገባ የቀረበው የንግድ ምልክት በአዋጁ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት እንዳይመዘገብ ለማድረግ መርማሪው ከሚከተሉት ቢያንስ አንዱን ከግምት ማስገባት ይኖርበታል፦

ሀ. ቀዳሚው የንግድ ምልክት በኢትዮጵያ ውስጥ ዝና ያለው ሲሆን፤

ለ. ለምዝገባ የቀረበው የንግድ ምልክት ከቀዳሚው ምልክት ጋር አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ሲሆን፤

ሐ. በቀዳሚው የንግድ ምልክት ዝና ያልተገባ ጥቅም ማግኘት ወይም

የቀዳሚው ንግድ ምልክት ባለቤት ጥቅም ላይ ጉዳት የሚደርስ ሲሆን፤ወይም

መ. ለምዝገባ የቀረበው የንግድ ምልክት በዕቃዎቹ ወይም በአገልግሎቶቹ መካከል ግንኙነት እንዳለ በማስመሰል ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ሲሆን ነው፡፡

28. ያለምዝገባ ጥቅም ላይ ስለዋሉ የንግድ ምልክቶች

1/ ኢትዮጵያ ውስጥ በጥቅም ላይ ከዋለ የንግድ ምልክት ጋር ተመሳሳይ ወይም አንድ ዓይነት የሆነ የንግድ ምልክት እንዲመዘገብ ለጽሕፈት ቤቱ የምዝገባ ማመልከቻ ሲቀርብ ጉዳዩ ይመለከተኛል በሚል ሰው ተቃውሞ ሊቀርብበት ይችላል፡፡

2/ እንዲመዘገብ የቀረበ የንግድ ምልክት ቀድሞ በጥቅም ላይ ከዋለ የንግድ ምልክት ጋር አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ከሆነ ማመልከቻው ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

3/ ቀዳሚ የንግድ ምልክት መብት ቀድሞ በማስመዝገብ የሚገኝ ሲሆን የቅድሚያ ተጠቃሚነት ደግሞ የንግድ ምልክቱን ለንግድ ተግባር ጥቅም ላይ በማዋል ቀዳሚ መሆንን ያመለክታል፡፡

4/ የንግድ ምልክት ባለቤትነት የሚገኘውና በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈጻሚነት የሚኖረው የንግድ ምልክት ምዝገባ የምስክር ወረቀት ሲሰጥ ይሆናል፡፡

5/ ያልተመዘገበ የንግድ ምልክት በኢትዮጵያ ውስጥ በጥቅም ላይ በማዋል ቀዳሚ ከሆነ ጥበቃ ያገኛል፡፡

6/ ሆኖም የቀዳሚ ተጠቃሚነት መብት የተጠየቀበት የንግድ ምልክት በአመልካቹ የምዝገባ ማመልከቻ ከቀረበበት ቀን በፊት የቅድሚያ ተጠቃሚነት አለኝ በሚለው ሰው ብቻ በቅን ልቦና ቢያንስ ለ3 ተከታታይ ዓመታት ጥቅም ላይ የዋለ መሆን አለበት፡፡

29. ስለታዋቂ የንግድምልክት

1/ በአዋጁ አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት አንድ የንግድ ምልክት በኢትዮጵያ ውስጥ ታዋቂ መሆኑንና አለመሆኑን የሚወስነው አግባብነት ያለው የህብረተሰብ

ክፍል ስለንግድ ምልክቱ ያለውን ዕውቀት እንዲሁም የንግድ ምልክቱን የማስተዋወቅ ሥራ በመሥራት ምክንያት የተገኘ ዕውቀት ጭምር ግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል፡፡



2/ የንግድ ምልክት ታዋቂ መሆን ወይም አለመሆኑን ለመወሰን ከዚህ በታች የተመለከቱ መስፈርቶችን መርማሪው ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡-

ሀ. የንግድ ምልክቱ አግባብ ባለው ህብረተሰብ ዕውቅና ያገኘበትን ደረጃ፤

ለ. የንግድ ምልክቱ ጥቅም ላይ የዋለበት ጊዜ፤

ሐ. ጥቅም ላይ የዋለበት ስፋትና የሚሸፍነው ስፍራ፤

መ. የንግድ ምልክቱ ጥቅም ላይ የዋለባቸው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ለምሳሌ፡-በንግድ ትርኢት ወይም ባዛር ላይ መቅረብ፣ማስታወቂያዎችን ጨምሮ ስለንግድ ምልክቱ የተደረገው የማስታወቅ ሥራ የፈጀው ጊዜ፣ የስራ ውስፋትና የሚሸፍነው ስፍራ፤

ሠ. የንግድ ምልክቱ ጥቅም ላይ የዋለ መሆኑን ወይም ዕውቅና የተሰጠው መሆኑን ለማሳየት የተፈጸሙ ምዝገባዎች ወይም የቀረቡ ማመልከቻዎች ጋር ተያይዞ የፈጀው ጊዜና የሚሸፍነው ስፍራ፤

ረ. በንግድ ምልክቱ የይገባኛል ጥያቄ ላይ ስኬታማ የመብት ማስከበር መኖሩን የሚያሳይ የተመዘገበ መረጃ በተለይ አግባብ ባላቸው አካላት የንግድ ምልክቱ በሚገባ ታዋቂ ለመሆኑ የሚያሳይ ሰነድ፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (3) ላይ በተዘረዘሩት መስፈርቶች መሠረት ታዋቂነትን ለመወሰን የእያንዳንዱ ጉዳይ ልዩ ባህሪይ እና አኳኋን ተለይቶ እየታየ ውሳኔ የሚሰጥ ይሆናል እንጂ ለሁሉም ጉዳዮች መስፈርቶቹ በተመሳሳይነት በአንድ ዓይነት ሁኔታ ለእያንዳንዱ ጉዳይ ተግባራዊ የሚሆኑ አይደሉም፡፡

4/ አግባብ ያለው የህብረተሰብ ክፍል የሚወሰንባቸው ሁኔታዎችን በሚመለከት ታሳቢ ከሚደረጉት ሁኔታዎች መካከል የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

ሀ. የንግድ ምልክቱ ጥቅም ላይ የዋለባቸውን ዕቃዎች እና/ወይም አገልግሎቶች እየተጠቀመ ያለ ወይም ሊጠቀም የሚችለው ህብረተሰብ፤

ለ. የንግድ ምልክቱ ጥቅም ላይ የዋለባቸው ዕቃዎች እና/ወይም አገልግሎቶች የንግድ ስርጭት መስመሮች፤

ሀ. የንግድ ምልክቱ ጥቅም ላይ የዋለባቸው ዕቃዎች እና/ወይም አገልግሎቶች በሕብረተሰብ ውስጥ ያላቸው የንግድ እንቅስቃሴ።



## ክፍል 5

## የማመልከቻ ምርመራ ውጤት

30. በቀረበ ማመልከቻ ላይ የሚሰጥ ውሳኔ

1/ መርማሪው የቀረበለትን የንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻ የፎርማሊቲና የሥረ ነገር ምርመራ በማድረግ የምርመራ ውጤቱን ለዳይሬክቶሬት ዳይሬክተሩ ማቅረብ አለበት።

2/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሠረት በቀረበለት ምርመራ የዳይሬክቶሬት ዳይሬክተሩ የንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻው ተቀባይነት የማይኖረው ከሆነ ማመልከቻው ተቀባይነት የሌለው መሆኑን የመርማሪው ውጤት በደረሰው በ10 ቀን ውስጥ በጽሑፍ ለአመልካቹ መስጠት አለበት።

31. የተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ ስለማውጣት

1/ በጋዜጣው ላይ የወጣው የማስታወቂያ ጥሪ ጽ/ቤቱ የማስታወቂያ ጥሪ እንዲወጣ በጽሑፍ ከገለጸው የተቀነሰ፣ የተለወጠ፣ የተጨመረ ወይም በጋዜጣ የወጣው የጥሪ ማስታወቂያ የማይታይ በመሆኑ ተቃውሞ ለማቅረብ የማያስችል ሆኖ ሲገኝ አመልካቹ የጥሪ ማስታወቂያው እንደገና እንዲወጣ ማድረግ አለበት።

2/ ስለሆነም የመጀመሪያ የጥሪ ማስታወቂያ የጊዜ ገደብ ተብሎ የሚቆጠረው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የጥሪ ማስታወቂያው ተስተካክሎ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ይሆናል።

32. የተቃውሞ ማመልከቻ ይዘትን በተመለከተ

የተቃውሞ ማመልከቻ ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በተደረገው እና ለዚሁ አላማ በተዘጋጀው ፎርም መሰረት ተዘጋጅቶ መቅረብ አለበት።

33. በተቃውሞ አቤቱታ ላይ ስለሚደረግ ምርመራ

1/ የዚህ መመሪያ አንቀጽ 37 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ጽ/ቤቱ ተቃውሞ እንደቀረበለት የተቃውሞ አቤቱታው በአግባቡ የቀረበ ስለመሆኑ ምርመራ ያደርጋል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተደነገገው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ መርማሪው በሚያደርገው ምርመራ ከዚህ በታች የተመለከቱት መስፈርቶች መሟላታቸውን ማረጋገጥ አለበት፦

ሀ. ተቃውሞው በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ የቀረበ መሆኑን፤

ለ. የተቃውሞ ምክንያቶቹ በአዋጁና በደንቡ መሠረት የቀረቡ መሆናቸውን፡፡

34. የንግድ ምልክት ምዝገባ አመልካች ሪፖርት ማድረግን በተመለከተ

ጽ/ቤቱ በደንቡ አንቀጽ 31(1) ድንጋጌ መሰረት የምዝገባውን ቀጣይ ሂደት ለማስቀጠል ይችል ዘንድ አመልካቹ የተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ የ60 ቀን ጊዜ እንዳለቀ የተቃውሞ ጥሪ የወጣበትን ጋዜጣ በመያዝ ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡

## ክፍል 6

## ስለ ንግድ ምልክት ምዝገባን ማሻሻል

*35. ምዝገባን ስለማሻሻል*

1/ በንግድ ምልክት ማመልከቻ ምዝገባ አፈጻጸም ላይ የተፈጠረ ስሕተት በደንቡ አንቀጽ 40 መሠረት የሚሻሻል ይሆናል፡፡

2/ በደንቡ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በተመለከቱት ምክንያቶች ምዝገባ እንዲሻሻል ማንኛውም አመልካች የምዝገባ ማሻሻያ ሲያቀርብ አመልካቹ በደንቡ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ (2) ሥር የተመለከቱትን ሁኔታዎች አሟልቶ ማመልከቻ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ በ30 የሥራ ቀናት ውስጥ ጽ/ቤቱ ማመልከቻውን መርምሮ የማሻሻያ ጥያቄው ውድቅ የማይሆንበት ምክንያት ካለ አዲስ የምስክር ወረቀት መስጠት ወይም ማመልከቻው ውድቅ የሚሆንበት ምክንያት ካለ ምክንያቱን በጽሑፍ መስጠት አለበት፡፡

3/ በደንቡ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ (1) ሥር በተመለከቱት ምክንያቶች ምዝገባው መሻሻል ያለበት መሆኑን ጽ/ቤቱ ሲያምን የማሻሻያ ምክንያቶችን በመዘርዘር ለንግድ ምልክት ባለቤቱ በሸኚ ደብዳቤ ይልክለታል፤ የንግድ ምልክት ባለቤቱም በማሻሻያው ላይ ያለውን አስተያየት የጽ/ቤቱ ደብዳቤ በደረሰው በሠላሳ ቀናት ውስጥ ያለውን

አስተያየት ለጽ/ቤቱ ማቅረብ አለበት፡፡

4/ ጽ/ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ማሻሻያ የተላከለት የንግድ ምልክት ባለቤት አስተያየቱን ካቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት 15 የሥራ ቀናት ውስጥ በምዝገባው ላይ ማሻሻያ ያደርጋል፡፡



5/ የንግድ ምልክት ባለቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) በተላከለት ማሻሻያ መሠረት አስተያየቱን ለጽ/ቤቱ ሳያቀርብ ቢቀርም ጽ/ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ላይ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ የምዝገባ ማሻሻያውን በማድረግ የተደረገውን ማሻሻያ በጽሑፍ ለንግድ ምልክት ባለቤቱ ያሳውቀዋል፡፡

36. የማመልከቻ ምርመራ በተለየ አኳኋን እንዲፈጸም ስለሚደረግበት ሁኔታ

የደንቡ አንቀጽ 24 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በዳይሬክቶሬቱ ውስጥ በሚገኙ መርማሪዎች የሚከናወነው የንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻ ምርመራ በተለየ አኳኋን መመርመር ይገባዋል ብሎ የጽ/ቤቱ ዋና ዳይሬክተር ሲያምን፡-

1/ በዳይሬክቶሬቱ ውስጥ ከሚገኙ ባለሙያዎች፤ ወይም

2/ ከዳይሬክቶሬቱ ውጭ ከሚገኙ የጽ/ቤቱ ባለሙያዎች፤የምርመራ ቡድን ወይም ኮሚቴ በማዋቀር የሚከናወነው ምርመራ እንዲቀጥል ወይም የተከናወነው ምርመራ እንደገና እንዲከናወን ለማድረግ ይችላል፡፡

## ክፍል 7

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

37. መረጃ ስለሚሰጥበት ሁኔታ

ከንግድ ምልክት ምስክር ወረቀት ወይም ከንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻ ምርመራ ጋር በተያያዘ ከፍትሕ አካላትና ከሌሎች ተቋሞች መረጃ፣ የሙያ አስተያየት እንዲሰጥ ወይም የባለሙያ ምስክርነት እንዲሰጥ ጥያቄ ሲቀርብ የንግድ ምልክት ዳይሬክቶሬት፣ የሕግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት፣ የአምሯዊ ንብረት ትሪቢዩናል እና እንደጉዳዩ አግባብነት የሚመለከታቸው ክፍሎች በአንድነትም ሆነ በተናጠል የተጠየቀውን መረጃ በተመለከተ ተገቢውን ትጋትና ጥረት በማድረግ በተቀላጠፈ ሁኔታ ጥያቄውን ላቀረበው የፍትሕ አካል ወይም ሌላ ተቋም አስተያየቱን ወይም መረጃውን መላክ አለበት፡፡

38. ተጠያቂነትን በተመለከተ

ከንግድ ምልክት ምዝገባ ሂደት ጋር በተገናኘ ማንኛውም ሰራተኛ አዋጁን፣ደንቡን፣ መመሪያዎችን እና ከህጉ ጋር የማይቃረኑ ልማዳዊ አሰራሮችን ሆን ብሎ እያወቀ ወይም ከፍ ባለ ቸልተኝነት በመጣስ ለሚፈፅመው ተግባር በዲሲፕሊን ተጠያቂ ይሆናል፡፡

39. ተፈጻሚነት ስለማይኖረው መመሪያ

የንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻ ምርመራን በሚመለከት ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ልማዳዊ አሰራሮችና ማናቸውም መመሪያዎች ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

40. የመመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከሚያዝያ 7 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

ኤርምያስ የማነብርሀን ኃይለማርያም